# ትንቢተ ኢዩኤል

## መግቢያ

### ጸሐፊው

ነቢዩ ኢዩኤል በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከሚገኙት ተመሳሳይ ስም ካላቸው ሌሎች ዐሥራ ሁለት ሰዎች ጋር አንድ አይደለም። ከኢዩኤል መጽሐፍና ከሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውጭ ስሙ አልተጠቀሰም (ሐሥ 2፥16)። ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ ስለ እርሱ የሚነገረው የፈጠራ ታሪክ የሚታመን አይደለም። አባቱም ባቱኤል (1፥1) የታወቀ ሰው አልነበረም። ስለ ይሁዳና ስለ እስራኤል ማሰቡን ስንመለከት (2፥32፤3፥1፡6፡8፡16-120 ይመ)፣ ኢዩ ኤል በዚያ አካባቢ የኖረ ይመስላል።

### የተጻፈበት ጊዜ

በመጽሐፉ ውስጥ የተከናወኑ ታሪካዊ ድርጊቶች ዘመናቸው አልተጠቀሰም፤ ይሁን እንጂ ይህ መጽሐፍ ከክርስቶስ ልደት በፊት በዘጠነኛው ምእተ ዓመት መጻፉን የሚያሳምን ብዙ ምክንያት አለ። ብዙ ተርጓሚዎች ደግሞ ይህ መጽሐፍ ከሐጌና ከዘካርያስ በኋላ፣ በስድስተኛው ምእተ ዓመት ይኸውም ከምርኮ ዘመን በኋላ እንደ ተጻፈ ይገምታሉ። ያም ሆነ ይህ የተጻፈበት ጊዜ በትክክል አለመታወቁ በመልእክቱ ላይ የሚፈጥረው ችግር የለም።

የኢዩኤል ትንቢት አጻጻፍ ከአሞጽ፣ ከሚክያስ፣ ከሶፎንያስ፣ ከኤርምያስና ከሕዝቅኤል ጋር የቋንቋ ተመሳሳይነት አለው። የእነዚህን መጻሕፍት ሥነ ጽሑፋዊ ተዛምዶ የሚወስነው የኢዩኤል መጽሐፍ የተጻፈበት ጊዜ ነው። ከላይ ከተጠቀሱት ነቢያት በፊት ተጽፎ ከሆነ እነርሱ ከኢዩኤል መጽሐፍ አባባል ተውሰዋል ማለት ነው፤ ከእነርሱ በኋላ ተጽፎ ከሆነ ደግሞ ኢዩኤል ከእነርሱ መጽሐፍ አባባል ተውሶአል ማለት ነው። አንዳንድ የሥነ መለኮት ምሁራን እንደሚሉት ነቢያት ሁሉ ይብዛም ይነስ በጊ ዜው እነርሱና ሕዝቡ በጋራ ከሚጠቀሙባቸው ሃይማኖታዊ ጽሑፎች በመቅዳት ተጠቅመዋል።

### መልእክቱ

ኢዩኤል፣ "ታላቁና አስፈሪው የጌታ ቀን" (2፥31) እንደሚመጣ በማመልከት፣ ይሁዳን የሚያጠ ፋውን አስከፊ ድርቅና ሰፍር ቍጥር የሌለውን ወራሪ አንበጣ አየ። በም 1፥4 እና 2፥25 የተጠቀሱት አንበጣዎች እውን አንበጦች እንጂ በምሳሌያዊ አገላለጽ ባቢሎንን፣ ሚዶ-ፋርስን፣ ግሪክንና ሮማውያ ንን የሚያመለክት አይደለም። ይህ ችግር በመጋረጡ፣ ኢዩኤል ሁሉንም ሰው፦ በዕድሜ የገፉትንና ወጣቶችን (1፥2-3)፣ ሰካራሞችን (1፥5)፣ ገበሬዎችንና (1፥11) ካህናትን (1፥13) ወደ ንስሐ ይጠራል፤ አንበጦችም የእግዚአብሔር ጦር ሰራዊት እንደ ሆኑና የእነርሱም መምጣት የጌታ ቀን መቅረቡን የሚያስታውስ መሆኑን ይገልጻል። ኢዩኤል ስለ እስራኤል ነጻ መውጣትና መባረክ እንጂ፣ ይህ ቀን በአሕዛብ ላይ ፍርድ የሚሰጥበት ጊዜ ይሆናል የሚለውን ሐሳብ አይገልጽም። ይልቁንም እንደ ኢሳይ ያስ (2፥10-21)፣ ኤርምያስ (4፥6)፣ አሞጽና (5፥18-20) ሶፎንያስ (1፥7-18) ሁሉ ይህ ቀን ታማኝ ሳልሆነችው እስራኤል የቅጣት ቀን እንደሚሆን ይናገራል።

### አስተዋፅኦ

1 ርእስ (1፥1)
2 በጌታ ቀን የሚሆነው ነገር ይሁዳ አሁን በተንሹ መቅመሷ (1፥2-2፥17)
  ሀ. እንዲያዝኑና እንዲጸልዩ የተደረገ ጥሪ (1፥2-14)
  ለ. ስለ ጌታ ቀን ምንነት መነገሩ (1፥15-2፥11)
  ሐ. ንስሓና ጸሎት እንዲደረግ የቀረበ ጥሪ (2፥12-17)
3 በጌታ ቀን ይሁዳ እንደምትድን የተሰጣት ማረጋገጫ (2፥18-3፥21)
  ሀ. እግዚአብሔር ይሁዳን ይጠግናል (2፥18-27)
  ለ. እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደገና ያድሳል (2፥28-32)
  ሐ. የጌታ ቀን መምጣት (ም 3)
    (1) በአሕዛብ ላይ የሚሆነው ፍርድ (3፥1-16)
    (2) የእግዚአብሔር ሕዝብ መባረክ (3፥17-21)

ፍርድ በሚሰጥበት ሸለቆ፣
*የእግዚአብሔር* ቀን ቀርቦአልና።
15 ፀሓይና ጨረቃ ይጨልማሉ፤
ከዋክብትም ከእንግዲህ አያበሩም።
16 *እግዚአብሔር* ከጽዮን ጮኾ ይናገራል፤
ከኢየሩሳሌም ያንጐደጕዳል፤
ሰማይና ምድርም ይናወጣሉ፤
*እግዚአብሔር* ግን ለሕዝቡ መሸሸጊያ፣
ለእስራኤልም ልጆች መጠጊያ ይሆናል።

## በረከት ለእግዚአብሔር ሕዝብ

17 "ከዚያም እኔ ስምባካቹሁ *እግዚአብሔር*፣
በቅዱሱ ተራራዬ በጽዮን እንደምኖር ታው
ቃላችሁ፤
ኢየሩሳሌም የተቀደሰች ትሆናለች፤
ከእንግዲህም ወዲያ ባዕዳን አይወሯትም።
18 "በዚያ ጊዜ ተራሮች፣ አዲስ የወይን ጠጅ
ያንጠባጥባሉ፤
ኰረብቶችም ወተት ያፈሳሉ፤
በይሁዳ ያሉ ሸለቆዎች[1] ሁሉ ውሃ ያጐርፋሉ፤
*ከእግዚአብሔር* ቤት ምንጭ ይፈልቃል፤
የሰጢምን ሸለቆ ያጠጣል።
19 ግብፅ ባድማ፣
ኤዶምም ምድረ በዳ ትሆናለች፤
በምድራቸው ንጹሕ ደም በማፍሰስ፣
በይሁዳ ሕዝብ ላይ ግፍ ፈጽመዋልና።
20 ይሁዳ ለዘላለም፣
ኢየሩሳሌምም ለትውልድ ሁሉ መኖሪያ
ትሆናለች፤
21 ደማቸውን እበቀላለሁ፤
በደለኛውንም ንጹሕ አላደርግም።"

## *እግዚአብሔር* በጽዮን ይኖራል!

3÷15 ኢዮ9÷7፤ ሕዝ32÷7
3÷16 መሳ5÷4፤ 2ሳሙ22÷3፤ ኢሳ14÷16፤25÷4፤42÷13፤ ኤር16÷19፤ ሕዝ38÷19፤ አሞ1÷2፤ ዘካ9÷12፤12÷8
3÷17 ዘፀ6÷7፤ መዝ2÷6፤74÷2፤ ኢሳ2÷2፤4÷3፤52÷1፤ ኤር31÷40፤ ሕዝ44÷9፤ ኢዩ2÷27፤ ዘካ9÷8
3÷18 ዘፀ3÷8፤ ዘፍ25÷1፤ መኃ5÷1፤ ኢሳ25÷6፤30÷25፤35÷6፤44÷3፤ ኤር31÷12፤ ሕዝ47÷1፤ ኢዩ2÷24፤ አሞ9÷13፤ ራእ22÷1-2
3÷19 ኢሳ11÷14፤19÷1፤34÷11፤51÷35፤ አብ1÷10 3÷20 ዕ ዝ9÷12፤ አሞ9÷15
3÷21 መዝ74÷2፤ ኢሳ1÷15፤59÷20፤ ሕዝ36÷25፤ 48÷35፤ ዘካ8÷3

[1]18 ወይም *የሺጢም ሸለቆ*

ነው። (ቍ.2:12) "ኢዮሣፍጥ" እግዚአብሔርን እንደ ዳኛ አድርጎ ይገልጠዋል (የቍ 2 ማብ ይመ)። ለየት ካለው የዕብራይስጥ ቃል የተወሰደው ይህ "ፍርድ" የሚለው፣ ቃል መለኮታዊ የፍርድ ውሳኔን ወይም የዳኛውን ትዕዛዝ የሚያመለክት ነው፤ እንግዲህ ሸለቆው ያ ፍርድ የሚፈጸምበት ስፍራ እንደ ሆነ ይገመታል።

*3÷15*፤ 2÷10 እና ማብ ይመ።

3÷16 *ጮኾ ይናገራል*፤ እግዚአብሔር እንደ አንበሳ ሕዝቦችን ይሰባብራቸዋል። የመጀመሪያዎቹ ሁለት ስንኞች በአሞ 1÷2 ላይ ይገኛሉ (ኤር 25÷30 ይመ)። *ያንጐደጕዳል*፤ እግዚአብሔር በሰራዊቱ አማካይነት በኢየሩሳሌም ላይ እንደ ሚያን ጐዳጐድ (2÷11)፣ እንዲሁም ርስቱን ከሚገዛበት ከመናገሻ ከተማው በኢየሩሳሌም ጠላቶች ላይ ያንጐደጕድባቸዋል። (ቍ.17፤ አሞ 1÷2 ይመ)።

*3÷17-21*፤ እግዚአብሔር ሕዝቡን በሁለት መንገድ ይባርካል፤ አሉታዊ በሆነ መልኩ ጠላቶቻቸውን በማጥፋት አዎንታዊ በሆነ መልኩ ደግሞ መልካም ነገሮችን በመስጠት ይባርካል።

3÷17 *እኔ...በጽዮን እንደምኖር*፤ እግዚአብሔር ራሱ ከእነርሱ ጋር ይኖራል (ቍ 21 ይመ)። ተመሳሳይ የሆነ አገላለጽ በ2÷27፤ በመዝ 46÷4 ላይ ይገኛል (ከራእ 21÷3 ጋር ያነጻጽሩ)። ያልተቀደሰችውና ለጥቃት የተጋለጠችው የአሁኗ ከተማ የመጨረሻ በረከት እግዚአብሔር በውስጧ መኖሩ ይሆናል (ቍ 21 እና ማብ፤ ራእይ 21 ይመ)። ከዚያም ከተማዪቱ ቅዱስና የማትበገር ትሆናለች።

3÷18 *በዚያ ጊዜ*፤ "በዚያ ዘመን" (ቍ 1) ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው። በዚህ ስፍራ የተገለጸው የዔድን ገነት ልምላሜ በ1÷10 ላይ ከተገለጸው ድርቅ ጋር የሚነጻጸር ነው (አሞ 9÷13 ይመ)። *ከእግዚአብሔር ቤት ምንጭ ይፈልቃል*፤ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሆነው የበረከት ምንጭ ሕዝቡን እያረሰረሰ ያለማቋረጥ ፍሬያማ እንዲሆን ያደርገዋል (ከመዝ 36÷8፤46÷4፤87÷7፤ ከመዝ 47÷1-12፤ ከራእ 22÷1-2 ጋር ያነጻጽሩ)። *የሰጢምን*፤ ሰጢም በደረቅ ዐፈር የበለጸገ ቢሆንም ሥዕላዊ መግለጫው በውሃ እንደተሞላ የሚያሳይ ነው።

3÷19 *ግብፅ...ኤዶምም*፤ የጥንት የእስራኤል ጠላቶች እንደመሆናቸው መጠን፣ በዚህ ስፍራም የእግዚአብሔርን ጠላቶች ሁሉ ይወክላሉ። *ባድማ...ምድረ በዳ*፤ ዘላቂ የሕይወት በረከቶች በሙሉ መወገዳቸውን የሚያመለክት ሲሆን፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ ዕጣ ፈንታና የእግዚአብሔር መንግሥት ጠላቶች ዕድል ምን ሊሆን እንደሚችል የሚያነጻጽር ዘይቤ ነው። በዚህ ስፍራ የተገለጸው ባድማነት ቀደም ብሎ የይሁዳ ሁኔታ ምን እንደነበረ የሚያስታውስ ነው (2÷3)።

3÷20 *ለዘላለም ... ሁሉ መኖሪያ ትሆናለች*፤ የእግዚአብሔር ፍርዱና ሕዝቡን መቤዠቱ በሚያበቃበት ጊዜ፣ መንግሥቱ ለዘላለም ያብባልና ጸንቶም ይኖራል።

*3÷21*፤ ይህ የፍርድ መጽሐፍ፣ "እግዚአብሔር በጽዮን ይኖራል" በሚል ተስፋ በሚሰጥና በሚያበረታታ ቃል ይደመደማል፤ ስለዚህም ከእርሱ ጋር ለሚኖሩና በእርሱ ለሚታመኑ፣ ሁሉም ነገር የተስተካከለና ቀና እንደሚሆን ያመለክታል።